## *የአክብሮትና የደስታ መልዕክት*

## *ለ41ኛ ኢሕአፓ ምስረታ*

ከተለያዩ አቅጣጫዎች እየተነዘሩበት ያለውን ድርጅቱን የማዳከም እርምጃዎችን በአባላቱ ከፍተኛ ንቃት ተቋቁሞ የዘንድሮውን የመጀመሪያ 41 ኛ የምስረታ በአሉን በሰሜን አሜሪካ ያላችሁት የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች በድምቀት ለማክበር በመዘጋጀታችሁ በተለያዩ አካባቢዎች ለምንገኘው አባላትና ደጋፊዎች ምንኛ ኩራት እየሰጠን እንዳለ የድርጅታችንን ማንነት፤ የአባላቱን ፅናትና ጥንካሬ የሚያውቁ የሚገነዘቡት ነውና ደስ ይበላችሁ አብረንም ደስ ይበለን እላለሁ።

በርግጥም 41 አመት በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ ቀላል አመት አይደለም። ድርጅታችን ኢሕአፓ የቆመለት አላማ ሕዝባችን ነፃነቱን በራሱ ትግል እንዲጎናፀፍና ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስከበር በዚህም በመመርኮዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅምና ሀገራዊ አንድነት በእኩልነት ጠብቆና አስጠብቆ ለተተኪው ትውልድ የሚተላለፍበትን ረግረግ ማመቻቸት እንደሆነ ግልፅ ነው። በመሆኑም በነዚህ አመታት የተደረጉትን እልህ አስጨራጭ ትግሎች ወደኋላ ዞር ብለን በሕሊናችን ስንቃኝ የግዴታ በትግሉ ሂደት በተለያዩ ደረጃዎች የተሰዉ አባላቶቻችንና ደጋፊዎቻችንን በዛሬው በድርጅታችን የምስረታ በአል አከባበር ቀን ከአዘቦት ለየት ባለ ሁናቴ ማስታወስ ለኛ ዋና ግዳጅ መሆኑ የሚጠበቅ ነው። ለዚህ ልዩ ምስጢር ኖሮት ሳይሆን ሰማዕታቱን የማያስታውስና ገድላቸውን የማይዘክር የፖለቲካ ድርጅት ተኪ የሌለው ብኩን ሆኖ ስለሚቀር ብቻ ነው። በበኩሌና ይህንን በአል ለማክበር የምትገኙ ሁሉ ኢትዮጵያዊነትና ኢሕአፓነት የዚህ ተቃራኒ ለመሆናቸው ታሪካቸው የሚመሰክርልን እንደሆነ ፅኑ እምነት አለኝ።

በዛሬው እለት ይህንን 41ኛ የምስረታ በአል ቀንን ስናከብር በየቦታው የሚሰነዘሩትንና የተሳሳተ መልስ እንድንሰጥ የሚጋብዙንና ከዋናው የትግል መስመራችን እንድንወጣ የሚያደርጉንን አጓጉል ጥያቄዎች ችላ በማለት ሆኖም ግን ያሳለፍነውን የትግል አመታት በአይነ ሕሊናችን ዞር ብለን በመመልከት፤ የትላንቱን በጥሞና ገምግመን የዛሬን ደግሞ በአርቆ አስተዋይነትና በእርጋታ እያየንና እየፈተንን፤ የነገንም አማትረን መሬት ሳንለቅ ገምተን የት ደርሰናል? ምንስ ማድረግ ይኖርብናል? ምንስ ማድረግ እንችላልን? ምንስ ይጠበቅብናል? የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች በጋራ የምንዳስሥበትም በመሆኑ ይህንን በያለንበት ተግባራዊ እንደምናደርገው ምንም ጥርጥር የለኝም። ተገቢውንም የተግባር መመሪያ እንደምንውስድም እንዲሁ ፅኑ እምነቴ ነው።

የዚህ አመት የምስረታ በአላችንን በጋራ በምናከብርበት ጊዜ ይህንን በአል ፍላጎታችን ተሳክቶ ሕዝባችን ነፃነቱን ተጎናፅፎ፤ የድሉን ፍሬ እየተቋደሰ፤ ሰላም በሰፈነበት ሁኔታ የሰማዕታቱ የቅርብ ዘመዶችና ወዳጆች በክብር እንግድነት በሚገኙበት እንዲሁም የድርጅቱ በርካታ አባላቱና ደጋፊዎቹ፡ ለድርጅታችን ቀናኢ የሆኑና የሱን ለድል መብቃት በጉጉት የሚጠባበቁ ሀገር ወዳድ ወገኖቻችን ሁሉ ሳይቀሩ በሚሳተፉበት የድርጅታችንን ምስረታ በአል ቀን ለማክበር እድሉን ብናገኝ እኔም ሆንኩ እናንተም የበአሉ ተሳታፊዎች የሚሰማንን ከፍተኛ ደስታ በቃላት ለመግለፅ የሚከብድ ነው ብል ሀቁን መናገር እንጂ ማጋነን አይሆንም። በበኩሌ ዛሬ ይህንን ቀን ስንዘክርና ስናከብር በኩራት ግዳጃቸውንና ትውልድ የጣለባቸውን ኃላፊነት ሲወጡ የተለዩንን ብርቅዬ ጓዶቻችንን አግባብነት ባለው መንፈስ እርምቻንን ለማውጣት እንኳ ሁኔታው አለመመቸቱን ሳስብ የኔም ሆነ የናንተም ሕሊና ክፉኛ ይቆስላል። ከኛ በበለጠ ደግሞ በሀገር ቤት የሚገኙትን የቅርብ ዘመዶቻቸውንና ጓደኞቻቸውን ሀዘንና ጭንቅ እንዲሁ ሳስብ ደግሞ ይበልጥ ያንገበግባል። ልብን ያቆስላል።

ከዚህ አንፃር ለምሳሌ የተከበሩ አቶ አብዲ አብዱላሂ ለሕትመት ባቀረቡት የ „ ያልታደለው ትውልድ“ መፅሃፋቸው ውስጥ ወ/ሮ አበበች ተረፈ የተባሉ የታጋይ እናት የተናገሩት ለዚህ ጉልህ ምሳሌ ነው። **“መቼም ለዚህ ያበቃን“** ይላሉ እኚህ እናት **„አምላክ የተመሰገነ ይሁንና ተደብቀን ሥሙን ለመጥራት የምንፈራው ኢሕአፓ እውነተኛ ነበር…እውነተኛ ነው ተብሎ ታሪኩን ለምሥክርነት እንዲህ መጠየቃችን እራሱ ትልቅ ዕድል ነው። አንተንም ደርግና መንግሥቱ ኃይለማሪያም ሳይሆኑ በዳኝነት ያተረፈህ እግዚአብሄር ነው። ይህንን እንድታይ…እኛ ተረስተን ተሰብረን የወደቅነውን.. ከየስርቻ ፈልገህ … አለሁ… እመሰከራለሁ… ኑ እንመስክር እንድትል ያበቃህ አምላክ እግዚአብሄር ይመስገን።“** በማለት ሕያው የምስክር ቃላቸውን ለታሪክ አስመዘገቡ። በዚህ ብቻ አላቆሙም። **„መሬቷን በእጃቸው ዳብሰው …እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው …“አቤት! … አቤት! ቸሩ መድሃኔአለም“ ብለው መሬቷን ሳም አደረጉ፡“** አቶ አብዲም በበኩላቸው የኝህን እናት የሰጡትን አስተያየት ካዳመጡ በኋላ **„ ይገርማል ኢሕአፓ የወጣቶችን አዕምሮ ብቻ ሳይሆን የወላጆችንም ልብ አብስሏል …እጅግ በጣም ገማችና እንደበተ ርቱዕ እናት ናቸው** ሲሉ በሳቸው አማካኝነት ሕዝብ ለኢሕአፓ ያለውን ከፍተኛ አድናቆት ከበፊቱ በበለጠ በቅርበት ሊያዩ አስችሏቸዋል። በርግጥም የልጃቸው የመለስ ጥላሁን መስዋዕትነትና እናቱም የሰጡት የምስክርነት ቃል ከላይ የገለፅነውን ቁም ነገር በሚገባ የሚመሰክር ሕያው ታሪካችን ነውና ምንጊዜም የማንረሳው ነው። የሳቸውና የልጃቸው መለሰ የመሰሉ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን አሁንም በሀገራችን በሕይወት ይኖራሉ። ረጅም እድሜም እንዲሰጣቸው እንመኛለን። የዛሬውም የምሥረታ በአላችን የነሱም ነውና በጋራ ደስ ይበለን የሚለው የደስታ መልዕክታችን ይድረሳቸው እላለሁ። ድርጅታችን ኢሕአፓ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ታሪኩን ለማደብዘዝ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች እየተቋቋመና እያስተካከለ ቢሆንም አሁንም ቢሆን ታሪክ እየሰራ ያለ በመሆኑና የቀድሞ ታሪኩን ምዕራፍ በምዕራፍ አቀናብሮ ለማቅረብ ትግሉ ለጊዜው ፋታ ባይሰጠውም ታሪኩን በራሱ አንደበት (ድርብ ሰረዝ ይጨመርበት) ለሕዝብ ማስነበቡ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ስኬታማ እንደሚሆን በበኩሌ ምንም ጥርጥር የለኝም።

ሁኔታዎች ተገጣጥመውለት ለሕዝብ ይፋ እስከሚያደርስ ድረስ ግን ሁሌም ደብዛቸው የጠፋውና ባጠቃላይ በተለያዩ አካባቢዎች በትግሉ ሂደት የተሰዉቱ አባላትና ደጋፊዎቻችን ምንጊዜም በሕሊናች ውስጥ ያሉ ብቻ ሳይሆኑ ከቶም መቼም ቢሆን ከቶ የማንረሳቸው ናቸው። የትግል ታሪካቸውንም ተተኪው ትውልድ ተረክቦ በእንክብካቤ በአርአያነት እንዲመለከታቸው ጥረታችንን እንቀጥላለን። በርግጥም አልሞቱም ሕያው ናቸው እያልን „የትግሉ ነው ሕይወቴ“ ዝማሬ እየዘመርን ልባዊ የክብር ምስጋና በዚህ የምስረታ በአል እንደገና ይድረሳቸው እያልን በቀየሱልን የትግል ጎዳና እንጓዛለን። ይህ ብቻ አይደለም። የነሱ መስዋዕት መሆን የዛሬ 41 አመት የጀመርነው ትግላችን ለስኬት እስከሚበቃ ድረስ እንደ ብረት የጠነከረ መሰረት ብቻ ሳይሆን ፅንተንም እንድታገል መቃብራቸው የማዕዘን ድንጋያችን ነውና እኛም ተራችን ደርሶ እስከምንገናኝ ድረስ በዚህ በዛሬው የምስረታ በአላችን አከባበር በጋራ አፈሩ ይቅለላቸው እንላለን። ከሁሉ በላይ ደግሞ በኛ ብቻ ሳይሆን በሕዝባችን ልብ ውስጥ የተቀረፀው ኃውልታቸው በሕሊናችን በተቀረፀ እቅፍ የፅጌረዳ አበባ የተጎነጎነ ነውና የሕያዊነት ብርሃኑን ምን ጊዜም እያበራ እስከ እለተሞታችን ድረስ የሚኖር መሆኑን በኩራት ስንገልፅ ደግሞ ደስታችን ወደር እንደሌለው ጠላት በሚገባ እንዲረዳው ያስፈልጋል።

ላለፉት ተከታታይ አመታት ከፊትም ከኋላ ከግራም ሆነ ከቀኝ ድርጅታችንን የተፈታተኑ ኃይሎች እንዳመጣጣቸው ተቋቁመን ውስጣዊ አንድነታችንንም አጠናክረን የተለያዩ ድርጅታዊ ሥራዎችና ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎችን በአውሮፓ፤ በአሜሪካና በሌላም ቦታዎች ለማካሄድ መቻላችን በርግጥም ለሚተናኮሱን ቅስም ሰባሪ ለወዳጆቻችንና ለደጋፊዎቻችን ደግሞ የሕዝብ አለኝታንታችንን አሁንም በተግባር እንደቀድሞው እናረጋግጣለን። ለምሳሌ በቅርቡ ድርጅታችን ኢሕአፓ ላቀረበው የሀገር አድን ጥሪ የተሰጠው ምላሽ የሚገልፀው ይህንኑ ነው። ድርጅታችንም በጥቅምት 24 ቀን 2006

ዓ.ም. ይፋ ባደረገው የምስጋና ደብዳቤ ከታዳሚዎቹ ጋር ያለውን የጠበቀ ግንኙነት በሚገባ የሚያመላክት እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም።

አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ቁም ነገር ታዳሚዎቹ የሰጡት ቀና ምላሽ ያለምክንያት እንዳልሆነ ነው። ኢሕአፓ መነሻውም መድረሻውም ኢትዮጵያዊነት ነውና ይህንን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለድርድር የማያቀርብ፤ ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ከሚዶልት ማንኛውም ኃይል ጋር የማይታበበር እንዲያውም ባለው አቅም ሁሉ የሚታገል እንደሆነ ባደረጋቸው ትግሎቹ ያረጋገጠላቸው በመሆኑና በዚህም እንደሚቀጥልበት የፀና እምነት ስላላቸው ብቻ ነው። የድርጅታችን ልሳን በሆነው ዴሞክራሲያ ቅጽ 37 ቁ. 7 ውስጥ እንደተገለፀው፦

*„ለዚህም ነው ሀገርን የማዳን ግዳጃችን ከዴሞክራሲ ሰንደቃችን ጋር አብሮ ተጣምሮ መዳዘን ማወቅና ማመን የሚገባን" መሆኑን* ከጠቆመ በኋላ በመቀጠል *„ ከዚህ ቀደም እንዳልነውም ሀገር ከሕዝቦች ውጭ የምትገለፅ ግዑዝ ክስተት አይደለችምና ታሪኳን በደማቸው ፅፈው መሰዋ ዕት ሆነው ህያውነቷን ያረጋገጡላትን*

*ልጆቿን ጠረን ማሽተት፤*

*መልካቸውን መምሰል፤*

*የልብ ትርታቸውን ማድመጥ፤*

*ራዕያቸውንም መኾን ይኖርበታል።*

*„እያንዳንዱ ትውልድ ፤ እያንዳንዱ ዜጋም ታሪክ የጣለበት ሀገራዊ ግዳጅ አለበት። ከእኛ በፊት የነበሩት የሀገራቸውን ጥሪ ሰምተው በዱር በገደሉ ከግዙፍ ጠላቶች ጋር በመዋደቅ ሸንፈትና ክህደት ኢትዮጵያዊነትን አይገልጡትም ብለው ሀገር አቆይተውልን አልፈዋል። ይህ ሊታለፍ የማይችል ከፅንቁ የከበረ የታሪክ ውርስ በእኛ ላይ ግዳጅ ስለሚጭን ወደ ሌላ ትውልድ የሚለጋ አይደለም። ከሀገር በላይ ምንምና ማንም የለምና እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሀገርን ለማዳን ዝግጁ ሆኖ በተጨባጭ ትግሉ ተሳታፊ እንዲሆን ከሚጠበቅበት በላይ ነን።"*

በማለት ያቀረበው አስተያየት በርግጥም ትላንትም፤ ዛሬም ወደፊትም የኛን ማንነት የሚገልፅና የተግባር መመሪያችንም በመሆኑ በተለይም ወጣቶች ይህንን ቁም ነገር ያለማቋረጥ እንዲገነዘቡት ማድረግ ወሳኝ የሚሆነውም በዚሁ ምክንያት ነው።

ታዲያ ዛሬም እንደ ቀድሞው ድርጅቱን እንደ አይን ብሌናቸው የሚንከባከቡ በርካታ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን አባላቱና ደጋፊዎቹም በድርጅቱ ውስጥ ብቅ እያሉ አንድነቱን ለመፈታተን የሚከጅላቸውን ሁሉ አጥብቀው እንደሚታገሏቸው ያልተገነዘቡ፤ ይህንን ቀና አስተሳሰቡን በመልካምነት የማይመለከቱ ሁሉ እንደፈለጋቸው ቢያቅራሩ፤ የፈለጋቸውን ሀሜታና ተንኮል ቢያሴሩበት የሚጠፉ፤ የሚዳከም እንዳልሆነ ብቻ ሳይሆን ድል አድራጊነቱን በተግባር እያረጋገጠ በመገኘቱ መቼም የማይፈርስ መሆኑን ሁሌም እያበሰረ የድል ችቦውኑም እያበራ ይገኛል። የወያኔ አገዛዝ በኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ባጠቃላይም በሕዝባችን ላይ በሚያካሂደው አስከፊ እመቃና አፈና እንዲሁም የተሳሳተ ታሪክን በማፃፍና በማሰራጨት የድርጅታችንን ሕልውና ቢፈታተንም፤ የተለያዩ መጠነ ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ሴራዎች ቢያስነዙበትም የሚጠፋ አልሆነም። ስለሆነም ኢሕአፓ አጥብቆ የሚታገላቸው መሆኑን በሚገባ ያውቁታልና ነጋ ጠባ የሱ መኖር ቅዠት በውስጣቸው እየለቀቀ ሲያቃዣቸውና ለተንኮል ተግባር ሲሰማሩ ማየቱ የሚገርመን አይሆንም።ይልቁንስ የሚያሳስበን የተገላቢጦሹ ቢሆን ነበር።

በተለይም ደግሞ ከታሪካችን ማህደር ውስጥ እውነታውን የሚገልፅ ሰነድ በጃችን የሌለና፤ ማንነታቸው የተደበቀም የሚመስላቸው ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ኢሚንት መሆኑን ቢያውቁና እየተጓዙበት ያለው ጎዳና የተሳሳተ መሆኑን ቢገነዘቡ የሚሻላቸው ይሆናል እንጂ የትግል ታሪካችን እንደሚያረጋግጠው ኢሕአፓን የሚያስበረግገው አይሆንም። ከሁሉም በላይ የድርጅቱን ታሪክ ጠንቅቀው የሚያውቁ ገና ከንዳቸውን ያልተንተራሱ በርካታና አሁንም ግዳጃቸውን እየተወጡ ናቸውና ባይቀናጡ ይበጃቸዋል። ይህንን ቀና ምክራችንን ለመስማት ጆሮአቸውን ከደፈኑማ አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነበት ወቅት የምንጠየፈውን የከፋ ድርጊታቸውንና ያደፈ ስማቸውን በመጥቀስ ለማጋለጥ ከበቂም በቂ ችሎታ እንዳለን በወሬ ሳይሆን በተግባር የምናረጋግጠው ነው። ይህ ደግም ዛቻና ማስፈራራት ሳይሆን ሀቁን መናገር እንጂ ሌላ አይደለም። ስለሆነም ይህን ምክራችንን ከወዲሁ ቢያዳምጡ መልካም ይሆናል። ለዚህም ነው ኢሕአፓ በነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓ.ም. የዛሬ 41 አመት ያወጀውን ሕልውናውን ጠብቆና ለሕዝብ የገባውንም ቃል ኪዳን እያከበረና እያስከበረ እስከዛሬ በቆራጥነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ኃይልና ተገን ሆኖ እየታገለ ነው ተብሎ አፅንዖት በተሞላበት አኳኋን የምንገልፀው። በርግጥም የሚያኮራ ታሪክ።

በበኩሌ የዚህ አኩሪ ታሪክ አካል ለሆኑ ሁሉ መልካም የበአል አከባበር ከደስታ ጋር እመኛለሁ።

በትግላችንን ኣንቸንፋለን!!

ኢሕአፓ ይለምለም!!

በርግጥም ኢሕአፓ ለወገኑ አለኝታ ለጠላቱ ደግሞ ቅስም ሰባሪነቱ ይቀጥላል!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

ዶር ዘነበ ተሾመ

ኮሎኝ ጀርመን

21.11.2013